
# በአርኪዎሎጂ[1] ቁፋሮ የተገኘ የአርባዕቱ እንስሳ[2] ቤተክርስቲያን ቅሪት

ተክሌ ሐጎስ*

## ፩. መግቢያ

ከ፲፱፻፺፯ - ፲፱፻፺፱ ዓ.ም በአክሱም ከተማ ልዩ ስሙ ጓንጓ እዳጋ እየተባለ በሚጠራው ቦታ ላይ የኢትዮጵያ ባህላዊ ቅርሶች ኘሮጀክት በመደበው በጀት እና ቁሳቁስ የአርኪዎሎጂ ቁፋሮ ተካሂዷል፡፡[3] የቁፋሮው ዓላማ ከአብርሃ ወአጽብሐ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ፊት ለፊት በስተምሥራቅ በኩል በሸቦ ታጥሮ በቆየው መካነ ቅርስ ውስጥ በጎርፍ ተሸርሽሮ የወጣውን ሕንፃ ምንነት አጥንቶ ለቀጣይ ልማት ማዘጋጀት ነው፤ ከዚህም በተጨማሪ ይህ የታጠረ ሰፊ ቦታ ቅርስ ያለበት መሆኑን ለአካባቢው ኅብረተሰብ በተጨባጭ ለማሳየትም በማሰብ ነው፡፡




የአርባዕቱ እንስሳ ቤተክርስቲያን የነበረበትን የሚያሳይ የአክሱም ከተማ ካርታ

*ተክሌ ሐጎስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የአርኪዎሎጂና የቅርስ አስተዳደር ትምህርት ክፍል መምህር ናቸው፡፡

[1] አርኪዎሎጂ ማለት የሰው ልጅ በምድር መኖር ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ ያለውን የቅድመ ታሪክ እና የታሪክ ዘመን፣ የሰው ልጆችን አኗኗር፣ ጠባይ፣ ባህል፣ ሥልጣኔ እና ከአካባቢያቸው ጋራ የነበራቸውን ግንኙነት ሳይንሳዊ በኾነ መልኩ የሚያጠና የዕውቀት ዘርፍ ነው፡፡ የአርኪዎሎጂ ምሁራን ከመሬት በላይም ኾነ ከመሬት በታች (በከርሠ ምድር) የሚገኙትን ቅሪቶች እና ቁሳዊ ግኝቶች በመተንተን እና በመተርጎም ሕይወት የሚሰጡ ናቸው፡፡

[2] አርባዕቱ እንስሳ የቅድስት ሥላሴን መንበር የሚሸከሙት ኪሩቤል እና ሱራፌል (ጸወርተ መንበር) ሲኾኑ በገጸ ሰብእ ፣ በገጸ አንበሳ ፣በገጸ ላሕም እና በገጸ ንስር የሚወከሉ የነገደ መላእክት ወገን ናቸው፡፡

[3] በዚህ የአርኪዎሎጂ ቁፋሮ ከዲላ ዩኒቨርስቲ፣ ከቅርስ ጥናት እና ጥበቃ ባለሥልጣን፣ ከአማራ ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ፣ ከትግራይ ባህል እና ቱሪዝም ቢሮ፣ ከአክሱም ማዘጋጃ ቤት እና ከአካባቢው ነዋሪዎች የተውጣጡ ሠላሳ ባለሞያዎች እና የቀን ሠራተኞች ተሳትፈዋል፡፡ለዚህ ጽሑፍ መነሻ ምክንያት የኾነውም በአክሱም ከተማ በተካኼደው የአርኪዎሎጂ ቁፋሮ የተገኘው የአርባዕቱ እንስሳ ቤተ ክርስቲያን ነው፡፡ የዚህ ጽሑፍ አቅራቢ በቁፋሮው ተግባር ላይ በመሪነት የነበሩ እና ግኝቱን አስመልክቶ መጽሐፍ ያበረከቱ ናቸው፡፡ ፣**መጽሐፉ** Tekle Hagos, 2008. *Archaeological Rescue Excavations at Aksum, 2005-2007*. Addis Ababa.

በአርኬዎሎጂያዊ ቁፋሮው በርካታ የአክሱም ዘመን የሥልጣኔ[4] ምስክር የኾኑ ቅርሶች ተገኝተዋል፡፡ በዚህ ጽሑፍ በቁፋሮ በተገኘው የአርባዕቱ እንስሳ ቤተክርስቲያን ላይ ብቻ በማተኮር አጠር ያለ ትንታኔ ይቀርባል፡፡

## ፪. ግኝት

በጥንት ጊዜ ጓንጓ እዳጋ እየተባለ በሚጠራው ቦታ ላይ አርባዕቱ እንስሳ የሚባል ቤተክርስቲያን እንደ ነበር በመጽሐፈ አክሱም[5] ላይ ሰፍሮ ይገኛል፤ የአካባቢው ነዋሪዎችም ይህንኑ ይናገራሉ፡፡ በ፲፱፻፮ ዓ.ም/እ.ኤ.አ/ ጀርመናውያን የሥነ ቅርስ ተመራማሪዎች በዚሁ ቦታ የአርባዕቱ እንስሳ ቤተክርስቲያን እንደ ነበር በዐይናቸው ማየታቸውን መስክረዋል፡፡ ተመራማሪዎቹ ቤተክርስቲያኑ ከጥንት ጊዜ ጀምሮ በአካባቢው የነበረ እና አርባዕቱ እንስሳ ተብሎ እንደሚጠራ የአካባቢውን ሕዝብ ጠይቀው መረዳታቸውን ተናግረዋል፤[6] እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስም አካባቢው አርባዕቱ እንስሳ እየተባለ ይጠራ እንደነበርም ለማወቅ ተችሏል፡፡

ከ፲፱፻፺፯ - ፲፱፻፺፱ ዓ.ም በዚህ ቦታ ላይ በተካሄደ የአርኪዎሎጂ ቁፋሮ በአክሱም ዘመን/ ከአንደኛው እስከ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን/ እና በ፲፱ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተሠሩ የቤተክርስቲያን ቅሪቶች ተገኝተዋል፡፡ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የተነሣ በቁፋሮ አማካይነት የወጣው ሕንፃ አርባዕቱ እንስሳ ተብሎ በጸሐፊው ተሰይሟል፡፡

በቁፋሮ የወጣው ሕንፃ ርዝመቱ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ፳፯ ሜትር፣ ጎኑ ከሰሜን ወደ ደቡብ ፲፫ ሜትር ኾኖ የአራት ማእዘን ቅርጽ አለው፡፡ ሕንፃው በግምት ፩.፲ ሜትር ከፍታ ባለው መሠረት ላይ የተገነባ ነው፡፡ መሠረቱ በከፊል በተጠረቡ ድንጋዮች እና በጭቃ የተሠራ ሲኾን የመሠረቱ አራት ማእዘናት በከፍተኛ ጥንቃቄ በተጠረቡ ታላላቅ ድንጋዮች የተገነባ ነው፡፡ የሥነ ሕንፃው ሥነ ውበትም በተጠረቡት የማእዘን ድንጋዮች ላይ የተመሠረተ ነው፡፡ በቁፋሮ የወጣው ሕንፃ ቤተክርስቲያን ከመቅደሱ፣ ቅድስቱ እና ከቅኔ ማሕሌቱ[7] ጋር ሌሎች አምስት እርስ በርስ የተያያዙ ክፍሎችም አሉት፡፡ በስተደቡብ በኩል ዕቃ ቤቱ ይገኛል፡፡


---

4 የአክሱም ዘመን ሥልጣኔ ከጌታ ልደት በኋላ ከአንደኛው መቶ ክፍለ ዘመን ገደማ ጀምሮ እስከ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ድረስ ያለውን የሚያጠቃልል ነው፡፡ ከጌታ ልደት በኋላ ከሦስተኛው እስከ ስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የአክሱም ሥልጣኔ ከፍተኛ ደረጃ ደርሶ እንደ ነበር መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡

5 "መጽሐፈ አክሱም" - በአክሱም ጽዮን ቤተ ክርስቲያን ዕቃ ቤት ብቻ የሚገኝ፣ ስለ አክሱም ታሪክ የሚናገር ትልቅ የብራና መጽሐፍ ነው፡፡

6 Tekle Hagos, pp. 4-5

7 በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ሥርዐት መሠረት አንድ ሕንፃ ቤተክርስቲያን ሦስት ክፍሎች አሉት፡፡ እነርሱም መቅደስ፣ ቅድስት እና ቅኔ ማሕሌት ይባላሉ፡፡ መቅደስ ሥልጣነ ክህነት ያላቸው (ዲያቆናት እና ቀሳውስት) ብቻ የሚገቡበት እና በሥርዐተ ቅዳሴ ጊዜ ሥጋ ወደሙ የሚፈተትበት ዋነኛው ወይም ማእከላዊው የቤተክርስቲያን ክፍል ነው፡፡ ቅድስት ደግሞ በቅኔ ማሕሌት እና በመቅደስ መካከል የሚገኝ ኾኖ በአብዛኛው ሥጋ ወደሙን የሚቀበሉ ምእመናን የሚያስቀድሱበት ክፍል ነው፡፡ ሦስተኛው ክፍል ቅኔ ማሕሌት ሲኾን ስሙ እንደሚያመለክተው በአንድ በኩል ሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ሥርዐተ ማሕሌት የሚፈጽሙበት፣ በሌላ በኩል ደግሞ ካህናት የሰዓታት ጸሎት የሚያደርሱበት እና በርካታ ምእመናንም የቅዳሴ ጸሎት የሚከታተሉበት ሰፊው ክፍል ነው፡፡



የአርባዕቱ እንስሳ ቤተክርስቲያን ኘላን

ከቤተክርስቲያኑ በስተምዕራብ የሚገኘው ሌላኛው ክፍል ርዝመቱ ከሰሜን ወደ ደቡብ ፱ ሜትር፣ ጎኑ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ፪. ሜትር ከ፳፬ ሴ.ሜ ነው፡፡ የዚህ ክፍል አራት ማእዘን ጥርብ ድንጋዮች በተለያዩ ጊዜያት ኾነ ተብሎ እንዲነሡ በመደረጋቸው ቤተክርስቲያኑ የመፈራረስ አደጋ አጋጥሞታል፡፡ ይህም ቤተክርስቲያኑ በሰው ሠራሽ ምክንያት ለመፍረሱ አስረጅ ሊኾን ይችላል፡፡

በዚሁ ክፍል በተደረገ ቁፋሮ ባለጥቁር ቀለም ሸክላዎች በብዛት የወጡ ሲኾን ይህም ካህናቱ ክፍሉን ምግብ ለማብሰያ[8] ይጠቀሙበት እንደ ነበር ሊጠቁም ይችላል፡፡ ቤተክርስቲያኑ አገልግሎት ካቆመ በኋላ ብርጭቆ ይሠራበት እንደ ነበር ለማረጋገጥ የሚያስችሉ በምርት ሂደት ላይ የነበሩ የብርጭቆ ስብርባሪዎች፣ የማምረቻ ምድጃ እና ሌሎች መረጃዎች ተገኝተዋል፡፡

የቤተክርስቲያኑ የሰሜን እና የደቡብ የውስጥ ግድግዳዎች ያንዳንዳቸው አራት ትይዩ የኾኑ ከግድግዳቸው ጋር ተያይዘው በድንጋይ ላይ የተገነቡ ምሰሶዎች አሉት፡፡ በስተሰሜን በኩል የሚገኘው ትልቁ የቤተ ክርስቲያኑ ክፍል /ቅኔ ማሕሌት/ ርዝመቱ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ፲፫ ሜትር ከ፴፫ ሴ.ሜትር ፣ ጎኑ ከሰሜን ወደ ደቡብ ፪ሜትር ከ፳፰ ሴ.ሜትር ነው፡፡ በስተምሥራቅ በኩል ከቅድስቱ ጋር ይገናኛል፡፡ ይህ ክፍል በተቃጠለ አመድ የተሞላ ሲኾን በውስጡም በርካታ የተቃጠሉ ጡቦች ተገኝተዋል፡፡

የቤተክርስቲያኑ መካከለኛው ክፍል/ቅድስት/ ርዝመቱ ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ፲፫ ሜትር ከ ፳፮ ሴ.ሜትር ፣ ጎኑ ከደቡብ ወደ ሰሜን ፫ ሜትር ከ፴፰ ሴ.ሜትር ነው፡፡ ይህም ክፍል በአመድ የተሞላ ሲኾን በውስጡም የተቃጠሉ ጡቦች ተገኝተዋል፡፡

በስተደቡብ በኩል ከቤተክርስቲያኑ ጋር ተያይዞ የሚገኘው ክፍል ከምሥራቅ ወደ ምዕራብ ፲፫ሜትር ከ፳፮ ሴ.ሜትር ርዝመት፣ ከሰሜን ወደ ደቡብ ፪ ሜትር ከ፳ ሴ.ሜትር የጎን ስፋት አለው፡፡ ይህም ክፍል በውስጡ ተገንብተው የወጡ አራት የደንጊያ ምሰሶዎች አሉት፡፡

[8] ለዚህ ዐይነት አገልግሎት የሚውለው ክፍል ቤተ ምርፋቅ በመባል ይታወቃል፡፡

የቤተክርስቲያኑ መቅደስ በሁለት የተለያዩ ዘመናት የተሠራ ሊኾን እንደሚችል ይገመታል፡፡ ጥንታዊው እና የመጀመርያው መቅደስ ከውጪው ግድግዳ ጋር የተያያዘ ኾኖ ከዕቃ ቤቱ በስተደቡብ ካለው የቤተ ክርስቲያኑ ክፍል ጋር ይገናኛል፡፡ እርሱም ከቤተክርስቲያኑ በስተምሥራቅ ይገኛል፡፡ መግቢያው በስተምዕራብ በኩል ሲኾን ስፋቱ ፩.፳ ሜትር፣ ወርዱ ፫.፶፰ ሜትር ነው፡፡ ከመሬት በታች ፩ ሜትር ከ፵፰ ሴ.ሜትር ጥልቀት ሲቆፈር መሠረቱ በተቃጠለ አመድ የተሞላ መኾኑ ተረጋግጧል፡፡

በ፲፱ኛው መቶ ክፍለ ዘመን የተሠራው የመቅደሱ ክፍል ደግሞ በከፊል የክብነት ቅርጽ ያለው ኾኖ በደንብ ባልተጠረቡ ጥቁር ድንጋዮች የተገነባ ነው፡፡ ፪ ሜትር ከ፸፫ ሴ.ሜትር ርዝመት፣ ፩ሜትር ከ፲ ሴ.ሜትር ጎን እና ፺፰ ሴ.ሜትር ከፍታ አለው፡፡ ይህም በ፲፱፻፺፮ ዓ.ም ጀርመናውያን ተመራማሪዎች ያዩትን የሕንፃ ቤተክርስቲያን ቅሪት ይመስላል፡፡ የቤተክርስቲያኑ ደቡባዊ ምሥራቅ ክፍል ከግምጃ ቤቱ በስተደቡብ የሚገኝ ኾኖ መግቢያው በስተደቡብ በኩል ነው፡፡ መሠረቱ ፩. ሜትር ከ፲ ሴ.ሜትር ጥልቀት ያለው ባለአራት ማእዘን ቅርጽ ሲኾን ስፋቱ ፬ ሜትር በ፫ ሜትር ነው፡፡ ከውጭ ወደዚሁ ክፍል የሚገባው በስተደቡብ አቅጣጫ ኾኖ መግቢያው ላይ የፈራረሱ ደረጃዎች ይገኙበታል፡፡



የቤተክርስቲያኑን የዕቃ ቤት መግቢያ የሚያሳይ ደረጃ

የቤተክርስቲያኑ ግምጃ ቤት በስተምሥራቅ በኩል ይገኛል፡፡ ርዝመቱ አራት ሜትር፣ ጎኑ ፪ ሜትር ከ፰ ሴ.ሜትር ሲኾን ቁመቱ ደግሞ ፪ ሜትር ከ.፷፰ ሴ.ሜትር ነው፡፡ መግቢያው ስምንት ደረጃዎች ያሉት ኾኖ ከጥቁር ጠፍጣፋ አንድ ወጥ ዐለት የተሠራ ነው፡፡ በዚሁ ክፍል የአክሱም ዘመን የመጸር መስቀል፣ ሳንቲሞች፣ ጠርሙሶች እና ባለጌጣጌጥ ሸክላዎች እንዲሁም አንድ ትልቅ ጋን በጥንት ጊዜ በተቀመጠበት ቦታ ተገኝቷል፡፡ በተጨማሪም በዚሁ ክፍል ሁለት የውስጥ መስኮቶች የተገኙ ሲኾን በልዩ ኹኔታ የተጌጡ ናቸው፤ በውስጣቸውም አነስተኛ የብረት ምስማሮች ተገኝተዋል፤ ውስጡም በነጭ ኖራ፣ በጭቃ እና በአነስተኛ ድንጋዮች በጥንቃቄ የተገነባ፣ ወለሉም በጠፍጣፋ ድንጋዮች በጥሩ ኹኔታ የተነጠፈ ነው፡፡

የአርባዕቱ እንስሳ ቤተክርስቲያን ከክርስቶስ ልደት በኋላ ከስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ እስከ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ባሉት ጊዜያት እንደተሠራ የሚጠቁሙ በርካታ መረጃዎች ይገኛሉ፡፡ በየዘመናቱ ከነበሩት የአብያተክርስቲያን ሥሪት በመነሣት ጥቂቶቹን ቅርጾች እንደሚከተለው ለማብራራት ይቻላል፡፡

የመቅደሱን ክፍል ቅርጽ በማየት የአርባዕቱ እንስሳ ቤተክርስቲያን የታነጸው ከስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን  አጋማሽ እስከ ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደኾነ ለመገመት ይቻላል፡፡ የመጀመርያዎቹ የኢትዮጵያ አብያተክርስቲያን መቅደስ ክፍል ክብ ወይም ባለ አራት ማእዘን ቅርጽ እንደ ነበሩ ከዚህ በፊት በተደረጉት ጥናቶች ተረጋግጧል፡፡

ከስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ ጀምሮ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን መቅደስ ቅርጽ ወደ ከፊል ክብነት መቀየር ጀመረ፡፡ በዚህ መረጃ መሠረት በቅርብ ጊዜ በቁፋሮ የወጣው የአርባዕቱ እንስሳ ቤተክርስቲያን በስድስተኛ መቶ ክፍለ ዘመን አጋማሽ እንደተሠራ መገመት ይቻላል፡፡ በአርባዕቱ እንስሳ ቤተክርስቲያን በአርኪዎሎጂ ቁፋሮ የተገኙት ሸክላዎች በስድስተኛው እና በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከተሠሩት የአክሱም ዘመን ሥልጣኔ ሸክላዎች ጋራ የሚመሳሰሉ ስለኾኑ በቁፋሮ የወጣው ቤተክርስቲያንም በዚህ የዕድሜ ክልል እንደተሠራ ተጨማሪ ማስረጃ ሊኾን ይችላል፡፡

የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ከአክሱም ከተማ ውጭ መስፋፋት የጀመረችው ዘጠኙ ቅዱሳን[9] ወደ አገራችን ከገቡበት ከስድስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በኋላ ነው፡፡ ከዚህ ክፍለ ዘመን በኋላ በአክሱም እና አካባቢዋ ከተሠሩት አብያተክርስቲያን አንዱ የአርባዕቱ እንስሳ ቤተክርስቲያን እንደኾነ ይገመታል፡፡

በአራተኛው እና በአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የክርስትና ሃይማኖት ምልክት የኾነው መስቀል በአክሱማውያን ሳንቲሞች ላይ መቀረጽ ጀምሯል፡፡ ይህ መስቀል በስድስተኛው እና በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን በአክሱማውያን ሕንፃዎች እና ሸክላዎች ላይ ጎልቶ መታየት የጀመረበት ወቅት ነበር፡፡[10] ከአርባዕቱ እንስሳ ቤተክርስቲያንም በቁፋሮ የወጡት ቅርሶች ይህን ሐቅ የሚያሳዩ ስለኾኑ ቤተክርስቲያኑም የታነፀው በዚሁ ክፍለ ዘመን እንደሚኾን መገመት ይቻላል፡፡

በአርባዕቱ እንስሳ ቤተክርስቲያን ዕቃ ቤት ውስጥ በቁፋሮ የተገኙት አንድ የመጾር መስቀል እና ሁለት የንጉሥ አርማሕ[11] ሳንቲሞች ቤተክርስቲያኑ በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን እንደተሠሩ የሚያሳዩ ናቸው፤በሁለቱም ሳንቲሞች ላይ የቃጠሎ ምልክት ይታይባቸዋል፡፡ በተቃጠለ አመድ እና ጡብ የተሞላው ቤተክርስቲያን የእርስ በርስ ጦርነት በተካሄደበት በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን  እንደፈረሰ መገመት ይቻላል፤ ይህም ቤተክርስቲያኑ ከተገነባ በኋላ ብዙም ሳይቆይ በቃጠሎ እንደወደመ ያመለክታል፡፡

[9] ዘጠኙ ቅዱሳን ከአምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መጨረሻ ጀምሮ ወደ ኢትዮጵያ እንደ መጡ ይነገራል፤ የመጡበትም ምክንያት እ.ኤ.አ. በ፬፻፶፩ ዓ.ም. በጉባኤ ኬልቄዶን የተወሰነውን የሁለት ባሕርይ እምነት አንቀበልም በማለታቸው በግሪክ - ሮም ዓለም (Greeko-Roman) መከራ ስለ ጸናባቸው መኾኑን መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ ዘጠኙ ቅዱሳን መንፈሳዊ መጻሕፍትን ከልዩ ልዩ ቋንቋዎች ወደ ግእዝ በመተርጎም፣ ገዳማዊ ሕይወትን እና ገዳማትን በአገራችን በመጀመር እና በማስፋፋት፣ አብያተክርስቲያንን በመገንባት እና በመሳሰሉት መንፈሳዊ ተግባራት ታላቅ አስተዋፅኦ አበርክተዋል፡፡ በመኾኑም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ውለታቸውን ባለመዘንጋት የቅድስና ማዕረግ ሰጥታ ታስታውሳቸዋለች፡፡

[10] Tekle Hagos, p.73-74

[11] ንጉሥ አርማሕ በሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን የነበረ የአክሱም ንጉሥ መኾኑ ይታወቃል፡፡

## ፫ *ማጠቃለያ*

ከ፲፱፻፺፯ - ፲፱፻፺፱ ዓ.ም በአክሱም ከተማ በተደረገው አርኪዮሎጂያዊ ቁፋሮ የተገኘው የአርባዕቱ እንስሳ ቤተክርስቲያን የመሠረት ቅሪት የአክሱም ዘመን ሥልጣኔ መለያ እና በዐይነቱም በዘመኑ የመጀመርያ የነበረ ነው፡፡ እስከ አሁን ድረስ በአክሱም ከተማ እና አካባቢዋ እንዲህ ዐይነት የቤተክርስቲያን ሕንፃ ቅሪት አልተገኘም፡፡ ለአክሱም እና አካባቢዋ ተጨማሪ መስሕብ የኾነው ይህ ታላቅ ታሪካዊ ቅርስ በአሁኑ ጊዜ በጥሩ ይዞታ ላይ ስለሚገኝ ባለበት ኹኔታ ጠብቆ ለምርምር እና የቱሪዝም ልማት ማዋል ተገቢ ነው፡፡

የአርባዕቱ እንስሳ ቤተክርስቲያን በስድስተኛው እና ሰባተኛው መቶ ክፍለ ዘመን መካከል የነበረውን ልዩ የሕንፃ ቤተክርስቲያን ጥበብ የሚወክል ብቸኛ መረጃ ነው፡፡ ኪነ ሕንፃው ከአራተኛው እስከ አምስተኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከነበረው የሕንፃ ቤተክርስቲያን አሠራር የቀጠለ መኾኑን መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ በስድስት አንድ ወጥ አሠራር -*ሦስቱ በሰሜን፣ ሦስቱ በደቡብ* - ተገንብተው በወጡ የድንጋይ ዓምዶች ላይ የቆመ ባለአንድ ፎቅ ሕንፃ እንደ ነበር ለመገመት ይቻላል፡፡ ስለኾነም በሕንፃ ጥበብ አሠራሩ፣ በታሪካዊ እና ባሕላዊ ፋይዳው ከፍተኛ ስለኾነ ልዩ ጥበቃ እና ክብካቤ እየተደረገለት ለቀጣዩ ትውልድ መተላለፍ ያለበት ቅርስ ነው፡፡